

# ኢየሱስ ከምድር ወደሰማይ ሄደ

* ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ከተነሳ በኋላ ለ40 ቀናት ለደቀመዛሙርቱ ተገልጦላቸዋል፡፡ ስለ እግዚአብሔር መንግስት ይነግራቸው ነበር፡፡

* አንድ ቀን በኢየሩሳሌም ሆነው የሚልክላቸውን ስጦታ እየተጠባበቁ እንዲቆዩ ያዛቸዋል፡፡ ያም ስጦታ መንፈስ ቅዱስ ነበር፡፡ በውስጣቸው እየኖረ ይመራቸዋል፡፡ ያፅናናቸዋል፡፡ ኢየሱስ እርሱ ለሰዎች ሁሉ እንደሞተ እንዲናገሩ እንደሚፈልግም ነገራቸው፡፡ ሰዎችን እንዲያስተምሩና የሚያምኑትንም እንዲያጠምቁ አዘዛቸው፡፡

* ይህን ካለ በኋላም አይናቸው እያየ ወደሰማይ ተወሰደ፡፡ ደመናም ከአይናቸው ሰወረው፡፡ እናም ነጭ ልብስ የለበሱ ሁለት መላዕክት አጠገባቸው ቆመው ነበር፡፡

* መላእክቱም “ ወደሰማይ የምትመለከቱት ምንድነው? ይህ ወደሰማይ የተወሰደው ኢየሱስ አንድ ቀን በተመሳሳይ መልኩ ተመልሶ ይመጣል፡፡” አሏቸው፡፡

* እኛም ኢየሱስ እንደገና ተመልሶ እንደሚመጣ እናምናለን፡፡

ይህ የኢየሱስ ወደሰማይ የመወሰድ ታሪክ የሚገኘው በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ 24፡ 50-53 እና በሐዋርያት ስራ ምዕራፍ 1፡ 1 – 11 ነው፡፡